በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

መጋቢት 19 ቀን 2011
አዲስ አበባ
መግለጫ

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከአገር ውስጥና ከውጭ ጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሾች

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለአገር ውስጥና ለውጭ ጋዜጠኞች ወቅታዊ የአገሪቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹ ነጥቦችም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

**የሕግ የበላይነትን ማስከበር በተመለከተ፤** በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተፈጥረው የነበሩ ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎችን መንግሥት እየተከታታለ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር ባለፈው አንድ ዓመት ተጠቃሽ ሥራዎችን ሰርቷል፡፡ ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደምሳሌ ያነሱት ከ30ሺ በላይ የታጠቀ ኃይል በነበረበት የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል የተፈጠረውን ቀውስ ከመቀልበስ ጀምሮ፤ በሐዋሳ፣ በቡራዩ፣ በአዲስ አበባ፣ በወለጋ፣ በሻሸመኔ፣ በጌዶና በቤኒሻንጉል በመቶዎች የሚቆጠሩ ተጠርጣሪዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት በመታየት ላይ መሆኑን ነው፡፡

**ኦዲፒና አዴፓን በተመለከተ፡** የቀድሞ ብአዴንና ኦህዴድ ኢህዴን በሚባል ንቅናቄ ውስጥ ታቅፈው ሲታገሉ የነበሩ እህት ድርጅቶች በመሆናቸው የጋራ ታሪክ እንዳላቸው ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በነዚህ ፓርቲዎች መካከል ረዥም ዘመን ያስቆጠረ አብሮ የመታገል ባህል እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ በኦዲፒና በአዴፓ መካካል ምንም ድንበር እንደሌለም ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ኢህአዴግ የመላእክት ስብስብ ባለመሆኑ በግለሰቦች በኩል ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡ የሐሳብ ልዩነቶቻችንን ወደውጭ በማውጣት በኩልም ልምምዳቸው ደካማ ስለሆነ ልዩነትን የማጉላት አዝማሚያ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳርና የኦሮሚያ ጉዳይን በተመለከተ፤** ጠቅላይ ሚኒስት ዐቢይ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት መሠረት ያለው መሆኑን አውስተው አንዱን ስናለማ ሌላውን አለመጉዳታችንን ልናስብበት እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡ በከተማ መስፋፋት ከ170 000 በላይ አርሶ አደር አባወራዎች እንደተፈናቀሉ ገልጸዋል፡፡ የአዲስ አበባ ጉዳይ የንትርክ አጀንዳ መሆን እንዳልነበረበትም ገልጸዋል፡፡ ችግሮች እንኳን ቢኖሩ መነጋገር እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል፡፡ ጽንፈኛ አቋም የያዙ ወገኖችን መድረክ አዘጋጅቶ ማወያየት የመገናኛ ብዙሃን ሥራ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያየዘ መንግሥትና ሕገ መንግሥት ባለበት አገር ምርጫ ሳይደረግ የሚኖር ራስን በራስ የመሾም ጉዳይ መፈንቅለ መንግሥት የሚመስል አካሄድ እንዳለም አውስተዋል፡፡

**የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ለውጥን በተመለከተ፤** ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደሥልጣን በመጡበት ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አረንቋ ውስጥ እንደነበር አውስተዋል፡፡ በተለይ የአገሪቱን የእዳ ሁኔታ አጽንኦት ሰጥተው ከጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥታቸው በሁሉም የዓለም ክፍል ባሉ አገራት ትኩረት አድርጎ ባደረገው ርብርብ ከአረንቋው መውጣት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

**ዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነትን በተመለከተ፤** ከአውሮፓ፣ ከሰሜን አሜሪካ፣ ከቻይና፣ ከመካከለኛው ምስራቅ አገራት በኩል ኢትዮጵያን ለመርዳትና ለማገዝ አገራቱና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል፤ በተግባርም እየረዱ ይገኛሉ፡፡ ይህ እርሳቸው ወደ ሥልጣን ከመጡ ወዲህ የተገኘ ስኬት እንደሆነም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ተናግረዋል፡፡ ዓመቱ የዓለም ሚዲያና ፖለቲከኞች ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ያሉበት እንደነበርም ገልጸዋል፡፡ ከጎረቤት የአፍሪካ ቀንድ አገራት ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት ተፈጥሯል ብለዋል፡፡ በአካባቢውም የኢትዮጵያ አሸማጋይነት የሚጠየቅበት እንደሆነም አውስተዋል፡፡

**የታላቁ ቤተ መንግሥትንና የአዲስ አበባ ማስዋብ ፕሮጀክትን በተመለከተ፤** የታላቁ ቤተመንግሥትን ወደ ፓርክና ሙዝየም የመቀየር ሥራ ለዜጎችና ለጎብኚዎች በቀላሉ የማይታይ የትምህርትና የመዝናኛ አገልግሎት እንደሚሰጥ የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወጪው 100% በዕርዳታ የሚሸፈን መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህም ሥራ ሲጠናቀቅ የሚሰጠውን ግልጋሎት በማሰብ በግል ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ የሚሰጣቸው እንደሆነ አሳውቀዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በርካታ አጋሮች ኢትዮጵያን ለማገዝ በትምህርት ቤት፣ በአረጋውያን ማዕከል ግንባታ እየሰሩ እንደሆነና የታላቁ ቤተ መንግሥት የፓርክና የሙዝየም ሥራ አንዱ እንደሆነ ለጋዜጠኞች ገልጸዋል፡፡ በቀዳማዊ እመቤት ጽ/ቤትም የዓይነ ሥውራንን ጨምሮ ታሪካዊ ሊባሉ የሚችሉ ትምህርት ቤቶችን የመገንባት ሥራ እየተሰሩ እንደሆነ አውስተዋል፡፡ አዲስ አበባን የማስዋብ ሥራም ባለሀብቶች አሻራቸውን የሚያኖሩበት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም ፕሮጀክት ለመሳተፍ ከኢትዮጵያውያን ባሻገር የውጭ አገራትም ፍላጎት እንዳሳዩ ጠቅሰዋል፡፡

//